
የእስልምና መሠረቶች

ለመዋዕለ ህፃናት (ለነርሰሪ)



ሳፊያ ኢቅባል

ትርጉም፡ በአህመድ የሱፍ

የእስልምና መሠረቶች

የእስልምና ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍ

ለመዋዕለ ህፃናት የሚሆን

ነርሰሪ



ሳፊያ ኢቅባል (MS, M.A., B.Ed.)

ርዕሰ መምህር

ዘ ስኮላር ትምህርት ቤት

ኒው ዴሊ

© አል-አስር ሀትመት

በዚሁ ደራሲ የተዘጋጁ ሌሎች መጽሐፍት፡-

- የእንግሊዘኛ ግጥም መማሪያ መጽሐፍት
- ሪትም ከክፍል 1 እስከ 9

የእስልምና ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍት፡-

- የእስልምና መሠረቶች፡ ከክፍል 1 እስከ 8 +
  የእስልምና መጀመሪያ እና ቅድመ-መጀመሪያ

የማኅበራዊ ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍት፡-

- የዓለም ታሪኮች፡ ከክፍል 1 እስከ 6
- ሴቶች እና የእስልምና ሕግ

ዓለም አቀፍ አከፋፋዮች፡-
አል-ሙታናቢ መጽሐፍ ቤት፣ ዱባይ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ


ስዕላዊ መግለጫ፡- ሲዛር ቦቴ

ንድፍ እና አቀማመጥ፡- ፊውቸርን ፕራይም፣ ዱባይ

- የመጀመሪያ እትም፡ 1996
- ሁለተኛ እትም፡ 1997
- ሦስተኛ እትም፡ 2010

አሳታሚ

- አል-አስር አሳታሚ
- ኢሜል፡ salabbhai@emirates.net እና dawood@mutanabbi.com



የአታሚው ማስታወሻ

ያለፈው ክፍለ ዘመን በባህላዊ መልኩ የተዘጋጁ የበለጸጉ ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎችን አስተናግዷል። የእነዚህ መጽሐፍት አባባፍ እና አቀራረብ እንደ ዘመኑ ፍላጎት ይለያያል። አሁን ግን በኤሌክትሮኒክስ እና በኮምፒዩተር ዓለም ውስጥ አዲስ ትውልድ አድጓል።

በመሆኑም በመጽሐፍት ዓለም ውስጥ አዲስ አቀራረብን ለማስተዋወቅ ጊዜው የደረሰ ይመስላል። ዛሬ ላይ ወጣቱን ትውልድ በዘመናዊ አውድ እና ድምጽ ሊያገኙ የሚችሉ እንዲሁም የዘመኑን ጥያቄ በሚፈለገው መልኩ የሚያቀርቡ መጽሐፍት እጥረት አለ።

በዚህ መሠረት አል-አስር ህትመት ሚዛናዊ እና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ለማፍራት የሚያስችሉ ዘመናዊ መጽሐፍትን የማዘጋጀት እና የማተም ሥራ ተረክቧል። የአንባቢያን ትኩረት ሊስቡ በሚችሉ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መጽሐፍትን ለማውጣትም አቅደናል።

ከመደበኛ ትምህርት በፊት ከመዋዕለ ህፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ድረስ ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመማሪያ መጽሐፍትን ለማዘጋጀት ሲባል ብቻ አንድ ልዩ ክፍል ተቋቁሟል። በእጃችሁ ያለው 'የእስልምና መሰረቶች' መጽሐፍ ለዝቅተኛ ፣ ለመካከለኛ እና ለከፍተኛ ክፍሎች በ10 ክፍሎች (ነርሰሪ ፣ መጀመሪያ እና ከክፍል 1-8) የተዘጋጀ ነው። ይህንን እንደ መጀመሪያ ህትመታችን በማቅረባችን ደስተኞች ነን።

በአርትኦት ሂደት የተቻለንን ብናደርግም አልፎ አልፎ የህትመት ስህተቶች ሊከሰቱ ስለሚችሉ በቀጣይ እትሞች የሚስተካከሉ የሆናል። ከማንኛውም አቅጣጫ የሚመጡ ትችቶችን እና አስተያየቶችን በደስታ እንቀበላለን። የእያንዳንዱን ህትመት ይዘት ጥራት በቀጣይ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ሲሆን ይህም መመሪያችን ተደርጎ በዘላቂነት የሚተገበር ይሆናል።

አሳታሚው

መቅድም

ይህ በ10 ክፍሎች የተዘጋጀ የእስልምና ጥናቶች መጽሐፍ ተከታታይ ፣ ለመረዳት ቀላል ፣ ሳቢና ማራኪ እና ሁሉን አቀፍ በሆነ አቀራረብ ተዘጋጅቷል። እነዚህ ተከታታይ መጽሐፍት ተማሪዎች እስልምናን እንደ አጠቃላይ የሕይወት ጎዳና እንጅ እንደ ባህላዊ እና ውስን የሕግጋት ስብስብ ብቻ እንዳያዩ ያስችላል።

እነዚህ መጽሐፍት አእምሮን እና ልብን ይማርካሉ። ሊያደርጓቸው የሚገቡ እና የማይገቡ ነገሮችን በምክንያታዊ መንገድ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ አላህን ወደሚፈራ ስብዕና የሚቀይሩ ልማዶችን እና ሥነ-ምግባራትን ያንጻሉ።

እነዚህ ተከታታይ መጽሐፍት መምህራን እና ወላጆች ለተማሪ ልጆቻቸው በትምህርት ቤትም ሆነ በቤት ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ማጣቀሻ እንደሚሆኗቸው ተስፋ እናደርጋለን።

በእጃችሁ ያለው ይህ ትንሽ መጽሐፍ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ታዳጊ ሕፃናትን በዙሪያቸው ባሉ ነገሮች እና ተግባራት አማካኝነት እስልምናን በቀለማት ባሸበረቀ መንገድ ያስተምራል። መምህሩ ይህንን መጽሐፍ ለዕለት ተዕለት የቃል ትምህርት እንደ ማጣቀሻ እንዲጠቀሙት ይመከራል።

የዚህ መጽሐፍ ስኬት የሚወሰነው አስተማሪዎች እና ወላጆች እያንዳንዱን ሃሳብ ከተማሪ ልጆቻቸው ጋር በመወያየት ፣ መረዳታቸውን ፣ መቀበላቸውን እና መፈፀማቸውን በማረጋገጥ ነው።


የመማር ማስተማር ሂደቱ ማወቅን ፣ መረዳት ፣ መቀበል እና በሃሳቡ ላይ መስራት ወይም መፈፀምን ያጠቃልላል። የእያንዳንዱ ትምህርት እና መልዕክት በልጆች ስብዕና ላይ ተዕዕኖ ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም በእለት ተዕለት ህይወታቸው ሃሳቡን ወደ ተግባር መቀየር ይኖርባቸዋል።

ሳፊያ ኢቅባል (ታህሳስ 2010)

ለመምህሩ የተሰጠ ማስታወሻ

1. ይህ መጽሐፍ ለቃል ጥናት ብቻ የታሰበ ነው።
2. ሕፃናት ጽሑፉን እንዲያነቡ አይጠበቅም። ይዘቱን በመምህሩ የዕለት ተዕለት ትምህርት ይማራሉ።
3. መምህሩ የዕለት ተዕለት የክፍል ትምህርቱን ለመከታተል ጽሑፉን እንደ ማጣቀሻ መጠቀም አለበት። ሕፃኑ ገና በፊደል ደረጃ ላይ ስለሆነ ጽሑፉን እንዲያነብ አታድርጉ።
4. በመጽሐፉ ውስጥ የተሰጡት 'ተግባራዊ ሥራዎች' ለማዳበር በየቀኑ በክፍል ውስጥ መለማመድ አለባቸው።
5. በእስልምና ጥናቶች ክፍለ ጊዜ ከተቻለ ጣፋጭ ነገሮችን ለልጆች አድሉ።
6. ከገጽ 7-13 ያሉት ለመጀመሪያው የትምህርት ዘመን ናቸው። ከገጽ 14-17 ያሉት ለሁለተኛው እና ከገጽ 18-20 ያሉት ለሦስተኛው የትምህርት ዘመን ናቸው።
7. ግጥሞችን ፣ ጥያቄዎችን እና ተግባራዊ ሥራዎችን በየቀኑ ወይም አንድ ቀን እየዘለሉ መከለስ በጣም አስፈላጊ ነው።


ስዕሉን ቀለም ቀቡ



ጥያቄ፡ ይህ ምንድን ነው?

መልስ፡ ቸኮሌት

ስዕሉን ቀለም ቀቡ




ጥያቄ፡ ይህ ምንድን ነው?

መልስ፡ አፕል

ጥያቄ፡ አፕልን የፈጠረው ማነው?

መልስ፡ አላህ

ስዕሉን ቀለም ቀቡ




ጥያቄ፡ ይህ ምንድን ነው?

መልስ፡ መጽሐፍ

ጥያቄ፡ መጽሐፉን የፈጠረው ማነው?

መልስ፡ አላህ

ስዕሉን ቀለም ቀቡ



ጥያቄ፡ ይህ ምንድን ነው?

መልስ፡ ቁርአን

ጥያቄ፡ በቁርአንን የፈጠረው ማነው?

መልስ፡ አላህ

እነዚህን ቃላቶች ከእኔ በኋላ ደግማችሁ በሉ

1. አላህ

2. ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላኂሁ አለይሂ ወሰለም)

3. እስልምና

4. ሙስሊም

5. ቢስሚላሂ አረህማኒ ረሂም

6. ሱብሐነላህ

7. አልሐምዱሊላህ

8. አላኂሁ አክበር

9. አሸሐዱ አላ ኢላሃ ኢለላህ

10. ቁርአን

11. ሐዲስ

የተግባር ልምምድ

1. ሰላምታ የምንለዋወጠው **አሰላሙ አለይኩም** በማለት ሲሆን መልሱ ደግሞ **ወአለይኩም ሰላም** ነው።

2. **ተክቢር**፡ አንድ ልጅ **ተክቢር** ይበል ሌሎቹ ደግሞ **አሏሁ አክበር** እንዲሉ አድርጉ። ልጆች በየተራ ተክቢር እንዲሉ አድርጉ።

3. ትዕዛዝ እንዴት መቀበል እንዳለባቸው አስተምሯቸው። ተቀመጡ ፣ ተነሱ ፣ እጅ ወደ ላይ አድርጉ ፣ እጅ ወደ ታች አድርጉ ፣ ተኙ ፣ ሂዱ ፣ ኑ ፣ መጽሐፋችሁን አውጡ ወ.ዘ.ተ

4. እንዴት እንደሚበሉ ማስተማር፡ እጃችሁን ታጠቡ ፣ በቀኝ እጃችሁ ብሉ ፣ ከመብላታችሁ በፊት **ቢስሚላህ በሉ**

5. ውሃ እንዴት እንደሚጠጡ ማስተማር፡ የውሃ ብርጭቆ ይዘው ቁጭ እንዲሉ በማድረግ **ቢስሚላህ** ይበሉ ፣ ውሃ ሲጠጡ በትንሽ በትንሹ ይጠጡ። ከጠጡ በኋላ **አልሐምዱሊላህ** ይበሉ።

6. በሱና መንገድ ፈገግ ማለት፡ ፈገግ በሉ። ጥርሳችሁን አታሳዩ። ከንፈራችሁ እንደተገጠሙ ፈገግ በሉ።

7. ለማመስገን ስትፈልጉ **ጀዛከላህ** በሉ።

<u>ማስታወሻ</u>፡ ውድ መምህራን ልጆች ከላይ ያሉትን በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ እንዲተገብሯቸው /እንዲሰሯቸው አድርጉ፡

ሊሸመድዷቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. ምንድን ነህ?

   መልስ፡ ሙስሊም ነኝ

2. የፈጠራችሁ ማነው

   መልስ፡ አላህ

3. እንዴት ናችሁ

   መልስ፡ አልሐምዱ ሊላህ

4. ሐዲስ ምንድን ነው

   መልስ፡ የነብዩ ንግግር


5. ስንት አምላክ ነው ያለው

   መልስ፡ አንድ ብቻ

6. አምላካችን እና ፈጣሪያችን ማን ነው

   መልስ፡ አላህ

ስዕሉን ቀለም ቀቡ



ጥያቄ፡ ይህ ምንድን ነው?

መልስ፡ አበባ

ጥያቄ፡ አበባን የፈጠረው ማን ነው?

መልስ፡ አላህ

የተግባር ልምምድ

1. ይህን ዱአ ሸምድዱ፡ ዱአ ለማድረግ እጃችሁን ከፍ አድርጉና **ረቢ ዚድኒ አልማ (ጌታየዋ እውቀት ጨምርልኝ)** በሉ፡፡
2. ምግብ ከበላችሁ በኋላ የሚባል ዱአ፡ ምግባችሁን በልታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ **አልሐምዱ ሊላሂ ለዚ አጥአምና ወሰቀና ወጀአልና ሚነል ሙስሊሚን** በሉ፡፡
3. እንዴት መቀመጥ አለባችሁ፡ ልጆች መቀመጥ ያለባቸው እጃቸውን ታፋቸው ላይ አድርገው እና እግራቸውን ገጥመው ፣ ከወገባቸው ቀጥ ብለው መሆን አለበት፡፡
4. ሲራመዱ፡ ልጆች ሲራመዱ ቀስ ብለው እንዲራመዱ አድርጉ፡፡ በልምምድ ወቅት እያንዳንዱ ልጅ የራሱን ተራ መጠቀም አለበት፡፡
5. ኢንሻአላህ ማለት፡ ልጆች ለሚሰሯቸው ስራዎች አዎ ወይም እሽ ከማለት ይልቅ **ኢንሻአላህ** እንዲሉ አስተምሯቸው፡፡

   ለምሳሌ፡ **ጥያቄ**፡ ነገ ትመጣላችሁ?

   መልስ፡ ኢንሻአላህ

   ጥያቄ፡ ወደ ጓደኛችሁ ቤት ትሄዳላችሁ?

   መልስ፡ አዎ ኢንሻአላህ

   ጥያቄ፡ መጽሐፉን ይዛችሁ ትመጣላችሁ?

   መልስ፡ ኢንሻ አላህ
6. ስትበሉ በቀኝ እጃችሁ ብሉ፡፡ ከመብላታችሁ በፊት **ቢስሚላህ** በሉ፡፡ ከበላችሁ በኋላም ዱአ አድርጉ፡፡
7. **ተክቢር በሉ** (ሁላችሁም በአንድ ላይ **አሏሁአክበር በሉ**)፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡ ከላይ ያሉትን ሃሳቦች መምህራን ክፍሉ ውስጥ ልጆች በድራማ መልክ እንዲለማመዱ በማድረግ አሳያቸው፡፡

ሊሸመድዷቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. ከሊማ (ሸሐዳ) በሉ?

   መልስ፡ ላኢላሃኢለሏህ ሙሐመደ ረሱሉሏህ

2. በጣም የሚወደን ማነው?

   መልስ፡ አሏህ

3. ቅዱስ መጽሐፋችሁ ምንድን ነው?

   መልስ፡ ቁርአን


4. ልንገዛው የሚገባ ማነው?

   መልስ፡ አሏህ

5. ጓደኞቻችሁ ጋር ትጫወታላችሁ?

   መልስ፡ አዎ ኢንሻአሏህ

ስዕሉን ቀለም ቀቡ



ጥያቄ፡ ይህ ምንድን ነው?

መልስ፡ ፀሐይ

ጥያቄ፡ ፀሐይን የፈጠረው ማነው?

መልስ፡ አላህ

የተግባር ልምምድ

ሀ. **ልማዶች፡** የሚከተሉትን ነገሮች ቢስሚላህ ካሉ በኋላ እንዴት መስራት (ማድረግ) እንዳለባቸው አስተምሯቸው፡፡

1. ፎጣ ማጠፍ
2. የጅ መሃረም ማጠፍ
3. ካልሲ እና ጫማ መልበስ
4. ጫማን ማሰር
5. ጥርስን መፋቅ
6. ፀጉርን ማበጠር
7. እጅን እና ፊትን መታጠብ (ወደ ቤት ከመሄዳቸው በፊት በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ)
8. የትምህርት ቤት ፖርሳ ማዘጋጀት
9. እርሳስ ወይም እስክርቢቶ አያያዝ
10. ቲሸርት መቀለፍ እና መፍታት
11. መጽሐፍ መግለጥ

ለ. ድምፃቸውን ከፍ አድርገው **ተክቢር** ይበሉ

ሐ. ጣፋጭ ነገሮችን አድሏቸው፡፡ ጣፋጩንም በቀኝ እጃቸው እንዲበሉ እና **ጀዛከሏህ** እንዲሉ አድርጉ፡፡

መ. **ጀዛከሏህ** አመሰግናለሁ ሲሉ **ባረከሏህ** ብላችሁ መልሱላቸው፡፡ ልጆቹም እርስ በርሳቸው እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡

ጥያቄዎች

1. ሱረቱል ፋቲሃን አንብቡ
2. ሱረቱል ኢህላስን አንብቡ
3. አንድ ሐዲስ አንብቡ

   መልስ፡ ንፅህና የኢማን ግማሽ ነው።።

የተግባር ልምምድ

የሚከተሉትን ነገሮች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ደጋግማችሁ ከልሱ

1. **አሰላሙ አለይኩም** እና መልሱ **ወአለይኩም አሰላም**
2. **ጀዛከሏህ** እና መልሱ **ባረከሏህ**
3. ትዕዛዞች፡ ቁሙ ፣ ተቀመጡ ፣ እጃችሁን ወደ ላይ እና ወደታች አድርጉ ፣ መጽሐፋችሁን ግለጡ ፣ ተሰለፉ
4. እንዴት እንደሚበሉ እና ውሃ እንዴት እንደሚጠጡ
5. እንዴት ፈገግ ማለት እንዳለባቸው
6. እንዴት እንደሚቀመጡ እና እንደሚራመዱ
7. **ቢስሚላህ** ማለት እና ፎጣ እና የእጅ መሃረም ማጠፍ ፣እና ጫማ መልበስ ፣ ጫማ ማሰር ፣ ጥርስን መፋቅ ፣ እጃቸውን እና ፊታቸውን መታጠብ ፣ ፀጉርን ማበጠር ፣ የትምህርት ቤት ፖርሳቸውን ማዘጋጀት እና መጽሐፍ መግለጥ
8. **የስንብት ክበብ ማዘጋጀት**፡ ልጆች ወደ ቤታቸው ከመሄዳቸው በፊት በየቀኑ ክብ ሰርተው እንዲቆሙ በማድረግ ረበና አቲና... (ዱአውን ጨርሱት) እንዲሉ እና ሰላምታ ተለዋውጠው ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ማድረግ።።ይህን ዱአ ልጆች መምህራቸውን ተከትለው ቃል በቃል እየደጋገሙ ማለት አለባቸው።።